# የትንሳኤው ጥሪ ለመሆኑ ለማን ነው?

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከላስ-ቬጋስ በሚተላለፍ ራዲዮ ጣቢያ ላይ ቃለ መጠይቅ የተደረገች የቀድሞ ኢሕአፓ አባል እህት ኢሕአፓን አንድ ማድረግ አለብን በሚል ያቀረበችውን ጥሪ አድምጬ መጨረሻውን ለማየት ስጠባበቅ ነበር። በነገራችን ላይ የዚህችኑ እህት ሌላ ቃለ መጠይቅ በጣሊያን ሀገር በሚተላለፍ የአማርኛ ፕሮግራም ላይ ተመሳሳይ ጥሪም አድርጋ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከዚህም ሌላ ሰሞኑን የተበተነች የትንሣኤ ቡድን በራሪ ወረቀት ሁለተኛዋን ቁጥር ደግሞ አግኝቼ አንብቤአታለሁ። በርግጥ በይዘት ከጥቂት ወራት በፊት አጠር ብላ ከተሰራጨችዋ ቁጥር አንድና ሁለተኛዋ ግራ ያጋባኝ ቢሆንም እስኪ ይህንኑ የመሰባሰብ ጉዳይ አስመልክቶ ያሉኝን ጥያቄዎችና ሃሳቦች እንደሚከተለው ለውይይት ላቅርብ። ከዚያ በፊት ከትንሣኤ ቁጥር 1 እና 2 ትንሽ ቀንጨብ አድርጌ ከዚህ በታች ለመንደርደሪያ እቅርቤአለሁ። በተለይም በበራሪዎቹና በቃለ መጠይቆቹ ውስጥ የተላለፉት መልዕክቶች ብዙ የሚያጠያይቁ ነገሮችና አባባሎችም ቢኖሩም እንኳን በእርግጥም ኢሕአፓን እንርዳው እስከሆነ ዋና መልዕክቱ ይሁንበት ብልም ከዚህ በታች ላሰመርኩባቸው አባባሎች ማብራሪያ ቢደረግልኝ ዓላማው ግልጽ ይሆንልኛል ብዬ እገምታለሁ።

***ከትንሣኤ ቁ 1፡-***

*"በቂ ዝግጅት ካደረግን በኃላ ሥብሠባ ተደርጎ በጋራ የምንሄድበትን አቅጣጫ የምንወስን መሆኑን ከወዲሁ እንድታዉቁት ይሁን። ይህንን ስብስብ እንድንፈጥር ካነሳሱን ዓላማዎች በጥቂቱ ፡*

*አሁን በመታገል ላይ ያሉትን የኢሕፓ አካሎችና ከዉጭ ያሉትን ቆራጥ የኢሕአፓ ልጆች መከፋፈሉ ቀርቶ ተሰባስበዉ ጠንካራ ኃይል ሆነዉ የሚወጡበትን ምንገድ ማመቻቸት።*

*በጥናት ላይ የተመሰረተ እስከተቻለ ድረስ ሁሉን ጓዶች እና ሁሉንም እካባቢዋች ያካተተ ታሪካችን እንዲጻፍ ማስተባበር የሚፅፉትንም መደገፍ።*

*በኢሕአፓ የትግል ታሪክና መታሰቢያዎች ዙራያ የሚሰሩ ሥራዋችን በመተባበር መሰራት።*

*በትግሉ መሰዋዓትነት የከፈሉትን ጓዶች የህይወት ታሪክ በማፈላለግና በማሰባሰብ ሥርዓት ባለዉ መልክ እንዲዘጋጁ ማድረግ ከሚያደርጉጋር መተባበርና መርዳት።*

*ድርጂታችን ባካሄደዉ ትግል የተለያዩ ፅሑፎችን (መፃህፍትና አርቲከሎችን)በመፃፍ የዚያን ጀግና ትዉልድ ታሪክ የሚያጠፉትን ኃይሎች መቋቋም።*

*በሃገራችን ጉዳይ ላይ መሰረት ያለዉ ዉይይት በማካሄድ የሃገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ አወንታዊ ኃይል ሆኖ ለመዉጣት መዘጋጀት።"*

*ከትንሣኤ ቁ 2፦*

*"ከዚህም ባሻገር የትንሥኤ ቡድን ሁሌም ኢሕአፓን አጠናክሮ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ እሱን ከመሳሰለ ጠንካራ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የጋራ ትግል እንዲያደርግም ይገፋፋል።ወቅቱ በጋራ መሥራትን አጥብቆ ይጠይቃልና።ሕዝቡም "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚለውን ጥሪ አሁንም እያቀረበ ነው፤ ለሕዝብ የሚሰራ ሁሉ የሕዝብን ድምፅ መስማት አለበት።በህዝብ ያልታቀፈና የሕዝብን ቃል የማያከብር ድርጅት ብቻዉን እነደቆመ ግንድ ነዉ። የሳለ መጥረቢያ በቀላሉ ይቆርጠዋል ለሕዝብ ለመቆም የሕዝብን ድምፅ መስማት፡የሕዝብን ፍላጎት ማወቅ፡ ያንንም ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል። ያለሕዝብ ድጋፍ ድርጅት ሊኖር አይችልም።ድጋፉን የሚሰጥ ሕዝብ ድምፁን የማሰማት መብት አለዉ የድርጅት መሪወች ይህንን ተገንዝበዉ መተባባር አለባቸዉ እልህ ግትርነትና በድርጅት ውስጥ ለራስ ከፍተኛ ቦታ መስጠት የተከፈለውን መስዋእትነት ያበላሻል። ልዩነትን በነጻ መድረክ ተወያይቶ መፍታት የግድ ባህልና የውዴታ ግዴታ መሆን አለበት። አባላትም መሪዎቻቸውን መከታተል የድርጅታቸውን ፖሊሲ መመርመር ልዩነትን ከማራገብ ይልቅ አንድነትን ማጠናከር ይኖርባቸዋል። በዚህ ዙሪያ ያሉትን ድክመቶቻችን ካስወገድን ኢህአፓን በማጠናከር ተባብሮ በመስራት የሕዝብን ትግል ከግብ ማድስ እንችል ይሆናል ብለን እናምናሆን።"*

እንግዲህ ከዚህ በላይ ያሉትን የትንሣኤ በራሪ ወረቀቶች ሳነብና ይህቺው እህታችን በራዲዮ ስለዚሁ ጉዳይ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላትና ካቀረበቻቸው ማብራሪያዎች በመነሳት የትንሳኤው ጥሪ ለመሆኑ ለማን ነው? የሚለው ጥያቄ በአዕምሮዬ መጉላላቱ አልቀረም። ትንሳኤ የሚለው ቃል ለክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ቤዛነት ከሞት መነሳትን የሚያመለክት ቃል ነውናም በኢሕአፓነት ትግሉን የቀጠሉት ወገኖች የዚያን ትውልድ አደራ ተቀብለው የተነሱበትን ዓላማ ሳያዛንፉ በጽናት ትግሉን መቀጠላቸውን ካልካድን በስተቀር የትንሣኤው ጥሪ እነሱን ይመለከታል ብዬ አልገመትኩም ነበር። እንደገባኝ የበራሪዎቹ መጣጥፎችም ሆነ የእህቴ ቃለ መጠይቆች መልዕክት ግን የትንሳኤው ጥሪ ለኢሕአፓ ስለሆነብኝ ማለቴ ነው። ታዲያ ጥሪው ለማንና ለምን? የሚሉ ጥያቆዎች ያነሳሁትም ለዚሁ ነው።

እንግዲህ የትንሳኤው ጥሪ በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅቱና ከትግሉ ራሳችንን አግልለን ለምንኖር (ከራሴ ጀምሮ) ዛሬ በቁጭት እህታችን እኛንም ራሷንም ለማነሳሳት ጥረት እያደረገች ከሆነ እሰየው የሚያሰኝ ነውና ሁላችንም እንደግፋታለን። ይሄ መልዕክት ግን ጥርት ብሎ አልወጣምና እንደ እኔ አይነቱ ጥሪው ለማን ነው ቢል አይፈረድበትም። ያም የሆነበት ምክንያት የትንሣኤው ንቅናቄ ዋና ገጽታ በመሆን በግንባር ቀደምነት እየተንቀሳቀሱ ያሉት ይህቺው እህትና አንድ ሌላ ወገን እንደመሆናቸው መጠንና የነሱንም ማንነት ሳጠያይቅ ያገኘሁት መልስ ከ 7 ዓመታት በፊት ተገንጥለው ከወጡት አንጃዎች መካከል መሆናቸውን ነው። እንዲያውም አንዳዶች ይህቺ እህታችን በጊዜው የድርጅት አባል ሳትሆን የቆየችና በጊዜው ለዚያ አንጃዎች ፈርጥጠው ለወጡበት ጠቅላላ ስብሰባ ቁጥር ማባዣ ከስብሰባው አለአግባብ እንድትገኝ አድርገዋት ከአንጃኛው ቡድን ጋር ተመልሳ የወጣች ነች የሚል ክስም

ያቀርቡባታል። ግድ የለም ምንም ትሁን ኢሕአፓን እናጠናክር ጥሪዋን በገንቢነት ልቀበለው ሳስብ በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ የኢሕአፓን እናጠናክር ጥሪ ወይስ የአዞ እንባ ወይም ደግሞ አሁንም ለፖለቲካ ፍጆታ የፈረደብንን ከውጭ ያለን ወገኖች ለመንዳት እየተሞከረ? የሚለው ጥያቄ በአዕምሮዬ ይጉላላል። ከዚህ በፊት ያጋለጥነውና ንቀነው የተውነው በሽታ ሌላ መልክ ይዞ እየመጣ ይሆን? ከዚህ በፊት ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ብለው ከድርጅታቸው ተለይተናል ሲሉንና ያቀርቡ የነበረውን ክስ ስንመረምር የብዙሃኑን ውሳኔ መቀበልና በዛ ውሳኔ መገዛት ያቃታቸው ውሁዳን እንደሆኑና በድርጅት ውስጥ የሚነሳን የሃሳብ ልዩነት በድምጽ ብልጫ የማሰናገድ ባሕልን የተጻረሩ ከመሆናቸውም በላይ፤ ለወዳጅም ሆነ ለጠላት "እኛ ዴሞክራሲያዊ ነን" ብለውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ተለይተው ሊያሳዩን ቃል ገብተው ብዙ ሳይቆዩ እርስ በእርሳቸው በዘር ሳይቀር ተናቁረውና ተረካክሰው ብትንትናቸው እንደወጣና ዛሬ እዚህ ግባ የሚባል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የሚጠቅም ሥራ ሲሠሩ ያልታዩ፤ ለመሆኑ የትንሣኤ ጥሪ ሲሉን ያ ያደረጉት የአንጃኝነት እንቅስቃሴ ድርጅቱን በማዳከም የተጫወቱትን ሚና ለመሆኑ አጥብቀው ተረድተውታል? ያስ ሲያቀነቅኑት የነበረው የቅራኔ አያያዝ አሁንም ትክክል ነው ብለው ያምናሉ? ወይስ ካላመኑ ለዚህ ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው ቅዱስ ዘመቻቸው ዛሬ እንዲታመኑ ያንን ድርጊታቸውን አውግዘው የሚነግሩን ነገር አለ? ከሌለስ እንደ እኔ አይነቱ በምን ይመናቸው?

"አሁን በመታገል ላይ ያሉትን የኢሕአፓ አካሎችና ከውጭ ያሉትን ቆራጥ የኢሕአፓ ልጆች መከፋፈሉ ቀርቶ ተሰባስበው ጠንካራ ኃይል ሆነው የሚወጡበትን መንገድ ማመቻቸት" ሲሉንስ ምንድርነው የሚሉን? መከፋፈሉ እኮ የመጣው አንጃኛው የዴሞክራሲያዊ አሠራርን አልቀበል ብሎ በቡድን አፍራሽ አቅጣጫ መከተሉ ብቻም ሳይሆን ውስጥ ለውስጥ ያሴረውም አጸያፊ ተግባርም ጭምር ነው። የድሮ የኢሕአፓ አካሎችስ ሲባል እነማንን ያመለክታል? ዛሬ እኮ ኢሕአፓ ነበርን ማለት የሚያፍሩና የሚሸሹም አሉ። ግማሹ ደግሞ በዘር የወያኔም ተላላፊም ሆኗል። በድርጅቱ ውስጥ የትግሉ ነው ሕይወቴን በልጅነት አብረን የዘመርነውንና፣ በአደራ የተቀበሉትን ይዘው የሚንገዛገዙ ወገኖችንና በራሳችን ፈቃድ ከውጭ የሕዝቡን ትግል ጣጥለን ላለፉት 35 ዓመታት የራሳችንን ኑሮ አደላድለን የምንኖረው እኮ ተወደደም ተጠላ ምንም ምክንያቶችን ብንደረድር ተለያይተናል። አዎን! እነዚህን ጓዶች እንርዳቸው ኢትዮጵያ ሀገራችን የኛም ነች ባስቸኳይ ያቅማችንን እናድርግ አንድ ትልቅ ቁም ነገር ነው። ያ ደግሞ የሚሆነው ዕውነተኛ መተማመንን በመካከላችንና በድርጅቱ ውስጥ ባሉ ወገኖቻችን በጥንቃቄ በገመገንባት ብቻ ነው። ከውጭ ተቀምጠን በትግል ላይ ያሉትን በማብጠልበል፣ ያለፉትን ሲቃይና የከፈሉትን መስዋዕትነት በማሳነስ አዙረን ለራስ ከፍተኛ ሥፍራ መስጠት ብሎ ማፌዝ ሊያቀራርበን አይችልም።

ስለታሪክም ቢሆን ሁሉም የአቅሙን ማሰባሰቡ ጥሩ ነው።ታሪክ ሲባል ደግሞ ሁሉንም የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባዋል። አንዳንዴ በየምክንያቱ ትግሉን ጥለን ከውጭ የተቀመጥን ወገኖች ኢሕአፓ ሲባል እኛ ጥለን እስከ ሄድን ድረስ አድርገን የመመልከት አባዜ ሲኖረን ያሳዝነኛል። በተለይ ደግሞ የታሪክ መረጃዎችን አሰባስበን ጻፍን የሚሉን በቅርቡ ሁለተኛውን መጽሐፍ በዋሺንግተን ለፊርማ ያቀረበውን ወገን እንኳ እንደምሳሌ ብወስድ (ያ ለአቶ ኢያሱ አለማየሁ "ኢሕአፓና ታሪኩ" ለሚለው ጽሑፋቸው መልስ በወያኔ ጋዜጣ ላይ ምኑም ከምኑ የማይገጣጠም ትችት ጽፎ ያዙኝ ልቀቁኝ አቶ በረከት ስምዖን አብሮ አደጌ ነው ብሎ ተረግርጎ መጽሐፉን ማሻሻጪያ ዓይነት ዘመቻ የጻፈው ወገን

ማለቴ ነው) ታሪክ እጽፋለሁ ብሎ መረጃ ለማሰባሰብ ቃለ መጠይቅ ያደረጋቸው ወገኖች እኮ የሚፈልገውን እንጂ የተነገረውን በመጽሐፉ አላሰፈረውም ብለውም የሚከሱት ሲሆን፣ በሚያሳዝን ሁናቴ ደግሞ ለመረጃም ቃለ መጠይቅ ያደረጋቸው ከ 35 ዓመታት በፊት በተለያየ ምክንያት ድርጅቱን ለቀው የወጡትን እንጂ እስከ ዛሬ በትግሉ ውስጥ የቀጠሉትን ጓዶች አንዴም ለማስረጃ ያልጠየቀ መሆኑ ነው። እንዲያው እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ ስለተባለ የተሟላ ታሪክ እንደማያደርገውም ሊታወቅ ይገባዋል። የታሪክ ሽሚያ ወይም ንግድ ነው የተያዘው ብለው ወገኖች ቢተቹበት አይገርምም። ብቻ እየተስተዋለ ነው ቁም ነገሩ። ታሪክ ደግሞ በሁለቱም ወገን እንደተሳለ ካራ ማለት ነው። እውነትና ሁሉን እንጻፍ ቢባል እያንዳንዳችን የተጫወትነው ሊፈተሽ ነው ማለት ነው። ያ ደግሞ ብዙ የጀግንነት ታሪክ የመኖሩን ያክል የሚያሳፍርም የክህደትና የሸሸቱም ሁሉም ሊወጣ ነው ማለት ነው።

ኢሕአፓን የምንረዳው እነእገሌና እገሌ ስላሉበት ወይም ስለሌሉበት ሳይሆን ድርጅቱ ባለው ኢትዮጵያዊ አጀንዳ መሆን አለበት። በበኩሌ ይህንን ድርጅት የምረዳው ድሮ ያለፍኩበት ድርጅት ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ ሀገር ወዳድ ዴሞክራቶች የተሰባሰቡበት ድርጅት ስለሆነና ከኢትዮጵያዊ አጀንዳቸው ዝንፍ እንደማይሉ ባከታታይ በተግባር በሚወስዳቸው አቋሞች ነው። ለዚህ ደግሞ ዛር ተንቀጥቅጦ ትላንት ድርጅቱን ለማዳከም የተለያየ ሻጥር ሲፈጽሙ የነበሩ ወገኖች ያ የሄዱበት ጎዳና ትግሉንና ድርጅቱን የጎዳ እንደነበር አምነውበት ግለ-ሂስ ማድረግ አቅቷቸው ዛሬም እንኳ በሚበትኑት ወረቀት በተዘዋዋሪ ድርጅቱ ተዳክሟል የሚል የዘመቻ መልዕክት የሚያስተጋባ የሚመስል ሽፍጥ፤ ያሰባስቡናል ብዬ የምጠብቀው ነገር አይደለም። ገና እንሰባሰብና እንወስን? በምኑ ስለምኑ ነው የምንወስነው። ድርጅቱን ለመርዳት ከሆነ ምንስ መሰባሰብ አስፈለገ? ከዚህ በፊት እኮ የድሮ ኢሕአፓዎችን ለማሰባሰብ ድርጅቱ በየመዋቅሩ በቅንነት የተሳተፈበት ጥረት (ለሳንዲያጎ ዓይነት ስብሰባ ያበቃንን የመሰባሰብ ጥረት ማለት ነው) እነማናቸው ይዘው የፈረጠጡት? በጊዜው ቢያንስ የመረዳጃ እድር እንኳ እናቋቁም ብለን ስንጮህ ፍርሻ እንዲሆን፣ ከተደበቁበት ብቅ ብለው መስኮት መድረክ ያሉንን አንዘነጋም። ዛሬም በዕውነት መተማመን ላይ ልብ ለልብ የምንያያዝበት መንገድ ካልፈጠርን እንዲያው ግልጽ ባልሆነ መንገድ መፍትሄ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም። እንዴ! ዃረ ትላንታና አልተወለድንም ወገን እየተስተዋለ እንጂ! ያገሬ ሰው ሲተርት "ሰው ከቆየ ከሚስቱ ይወልዳል" ይላል። መቆየት ብዙ መንዘላዘል እያሳየን ነው። 35 ዓመት ከትግሉ ርቆ በትኖን የሄደውስ ክፍሉ ታደሰ ሰሞኑን የኢሕአፓን 42ኛ ዓመት ለማክበር በሚል በፍርሻ የምናውቃቸው እንደ መስቀል ወፍ ብቅ የሚያደርጓት አበራሽ በርታ የፓልቶክ መድረካቸው ከፍተው ሲቀልዱብን ውለው የለ? አዎን በክብር እንግድነትም እነ መላኩ ተነኘ ዓይነቱን አቅርበው (መላኩ ወያኔ ወደ ሥልጣን ከወጣ በኋላ ወያኔ ዴሞክራት ነው አትንኩብኝ ብሎ በየ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሲራቀቅብን የነበረ ነው እንደገና በዚሁ ፓልቶክ ኢሕአፓ ፈርሶ በአዲስ መልክ መደራጀት አለበት ብሎ ሳያፍር አፉን የሚከፍት ዓይነቶች ተሰባስበው) ሌሎችም የተሰለፉበት በአሁኑ ወቅት በድርጅቱ ውስጥ እየታገሉ ያሉትን አግልሎ ሆያ ሆዬ ስለተባለ "አሁን በመታገል ላይ ያሉትን የኢሕአፓ አካሎችና ከውጭ ያሉትን ቆራጥ የኢሕአፓ ልጆች መከፋፈሉ ቀርቶ ተሰባስበው ጠንካራ ኃይል ሆነው የሚወጡበትን መንገድ ማመቻቸት" ተብሎ ስለተጻፈ መቀራረብ ይመጣል ማለት አይደለም። ይልቁንስ ይህቺን እህቴንም ሆነ መሰሎቿን ራሴንም ጭምር ከድርጅቱና ከትግሉ ውጪ ያለን ወገኖችን የማሳስበው ኢሕአፓን ለመርዳት ከልብ ከፈለግን ማንም ሊያስቆመን

የሚችል ኃይል የለም። ያንን ጥረት መጀመር ያለብን ግን ግን ከራሳችን መሆን አለበት።  ድርጅቱ በተሳሳተ አቅጣጫም እንኳን እየተጓዘ ከሆነ ያንን ለማስተካከል እኛ ተሰባስበን ጠንካራ ኃይል ሆነን በመውጣት በድርጅቱ አባላት ተሰሚነትና ተከባሪነት ቦታን ስንይዝ እኮ ነው አምነውን ለምናቀርበውም ገንቢ ሂስ ቦታ ሊሰጡት የሚችሉት። ሚዛንም ያለው ሥራ መሥራት የሚቻለው ያኔ ነው። በባዶአችን የፍርሻና የሽሽት ታሪክ ይዘን በምን የሞራል ብቃታችን ነው ታዲያ ኢሕአፓን እናጠናክር ብለን ስለኢሕአፓ ድክመት ብዙ የምንፎክረው? ታዲያ ይሄም ራሱ በአንዱ በራሪ ወረቀት እንደተጠቆመው ለራስ ከፍተኛ ቦታ እየሰጠ ያለው ማን እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ አያሳየንም? ራሳችንን ከሰቀልንበት ማማ ላይ ወደ መሬት ወረድ አድርገን እኛ የዚያ ትውልድ ወገን ነን ብለን የምንመፃደቅበትን ወደ ጎን አስቀምጠን ራሳችንን ብንመረምር መልካም ነው ባይ ነኝ። ኢሕአፓን ለመርዳት ብዙ ምክንያት ባንደረድር፣ ከሕዝብ ትግል ወግነን የምንታገልበትን ሳናመነታ ብንወስን መልካም ነው ባይ ነኝ። እውነተኞቹ አሕአፓዎች እንደሆን እኛ ከጎናቸው ተሰለፍልን አልተሰለፍን ትግሉን ቀጥለዋል። ብዙዎቻችን ጥለናቸው ከሄድን በኋላ በብዙ ውጣ ውረድ፣ በብዙ መስዋዕትነት ፣ የዚያን ትውልድ አደራ ይዘው እንደቀጠሉ ነው። ያንንም ሲያደርጉ ቅድሚያቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሆነ የሚያውቁትን የድክመታችንን፣ የሽሽታችንን ፣ የክህደቶቻችንን እኛን ለማሳጣት ሲፖፖጡ አይታዩም። እርዱን ያኔ በልጅነት የተዋደቃችሁለትን ሕዝባዊ ሥርዓት እንመሥርት ከማለት በስተቀር። ብዙ ሳናወራ እንርዳቸው! የተግባር ሰዎች እንሁን!

አቶሰውየው ከሰሜን አሜሪካ

ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው!